# አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

# UNITY FOR DEMOCRACY AND JUSTICE PARTY (UDJ)

## የመድረክ መለስተኛ ፕሮግራም በሚመለከት ለቀረበ አስተያየት የተሰጠ ማብራሪያ

*መድረክ መለስተኛ ፕሮግራሙንና መተዳደሪያ ደንቡን ለማዘጋጀት ሠላሳ ሰባት ስብሰባዎችን አካሂዷል። እነዚህም ስብሰባዎች ከየካቲት ወር 2001 እስከ ነሐሴ 2001 ድረስ የተካሄዱ ናቸው። ሠላሳ ሰባቱም ስብሰባዎች የተመዘገቡ ከመሆናቸው በላይ ቃለ ጉባኤው በፓርቲው ጽ/ቤት ይገኛሉ። በፓርቲዎች መካከል የተደረሱባቸው ስምምነቶችና ልዩነቶች ተመዝግበው ተይዘዋል። መለስተኛ ፕሮግራሙ የያዘው የስምምነት አንቀፆችን ብቻ ነው። ከዚህ አጠቃላይ ሃሳብና ከቃለ ጉባኤው ላይ በመመስረት አንድነት በልዩነት ያስቀመጠውንና ከእናንተ በኩል ደግሞ ማብራሪያና አስተያየት እንዲሰጥባቸው ለተነሱ ነጥቦችን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።*

### 1. *የፌዴራል አወቃቀርን በተመለከተ:-*

*በማብራሪያው እንደተጠቀሰው ሁሉ በመለስተኛ ፕሮግራሙ መግቢያ ላይ በገጽ 8 የተገለፀው ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ ጥያቄ ማንሳቱ የሚገባ ነው። ስለዚህም ማብራሪያው እንደሚከተለው ነው።*

*ሁሉም የመድረክ አባል ፓርቲዎች አንድነትን ጨምሮ የመንግሥት አደረጃጀት ፌዴራላዊ መሆኑን ይቀበላሉ። አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የፌዴራል አወቃቀሩ መስፈርቶች መልከዐ-ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሰፋፈርን፣ አስተዳደራዊና የልማት (ኢኮሚያዊ) አመችነትን፣ ቋንቋን፣ ባህልን፣ ታሪክን ሌሎች ማህበራዊ ትስስሮችን የተከተለ መሆን አለበት ብሎ እንደሚያምን ግልጽ አድርጎ ልዩነቱን አስቀምጧል።*

### 2. *የብሔር ብሔረሰብ መብትና የግለሰብ መብት:-*

*በአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራም እንደተገለፀው ሁሉ አሁንም የግለሰብ መብት የመብቶች ሁሉ ቀዳሚ ነው። የግለሰብ መብት ከቡድን መብቶች ጋር እንዳይጋጭ ተገቢው ርመጃ ይወስዳል እንጂ ግጭቱን ለማምለጥ ካልተቻለ ለግለሰብ መብት ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል። የሕዝብ ውክልና አለው የሚባል አንድ ቡድን ወይም ተቋም ዴሞክራሲያዊ*

ሊሆን የሚችለው የግለሰብን መብት የዴሞክራሲ መሠረት አድርጎ ሲቀበልና ሥራ ላይ ሲያውል ነው፡፡ ለሰው ልጅ ግለሰባዊ መብት የተሟላ ክብር መስጠት ሲቻል ነው ዴሞክራሲ ሰፍኗል የሚባለው፡፡

የግለሰብ መብትን ለቡድን መብት መቀማት ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም ለብዙሃን ጥቅም ሲባል የግለሰብ ጥቅም መከልከል ከተጀመረ ብዙሃን የሚባሉትም ተራ በተራ መብት ወደማጣት ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ «የግለሰብ ነፃነት ቀዳሚ ስፍራ ይይዛል» ብሎ እንደሚያምን ግልጽ አድርጎ ልዩነቱን አስቀምጧል፡፡

## <u>የቡድን መብቶች</u>፡-

*ምንም እንኳን የአንድ ማህበረሰብ የመጨረሻ ግብ የእያንዳንዱ፤ የማህበረሰብ አባል ግለሰብ ነፃነትና መብቶች ሳይጓደሉ እንዲከበሩ ማድረግ ቢሆንም የተወሰኑ የማህበረሰቡ አባላት በጋራ የሚፈልጓቸውና እንዲከበሩላቸው የሚጠይቋቸው መብቶች እንዳሏቸው ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ እነዚህ የአንድ ማህበረሰብ የተወሰኑ ክፍሎች የጋራ መብቶች የግለሰብን ነፃነት በማይሸረሽርና አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ መከበር እንደሚገባቸው መድረክ ያምናል ፡- ከገጽ7-8*

የቡድን መብት ሲባል የብሔር በሔረሰቦች የሴቶች፤ የህፃናት፤ የሙያ ማህበራት ወዘተ ማለት ነው፡፡ ዴሞክራሲ በግለሰቦችና ማህበረሰቦች መካከል ላለው ልዩነት ዋጋና ግምት ይሰጣል፡፡ ልዩነት ያሉት ህብረ ብሔር፤ ህብረተሰብ መፍጠር ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ነው፡፡

## 3. <u>ከአማርኛ ሌላ ሁለተኛ ብሔራዊ ቋንቋን በሚመለከት</u>

*በመሠረቱ በአንድነት ፕሮግራም ውስጥ በገጽ 8 በፊደል መ ሥር «አማርኛ የፌዴራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ በህዝብ ውሳኔ ሲፀድቅ ሌላ ተጨማሪ የሥራ ቋንቋ እንዲኖር ይደረጋል» የሚለውና በመድረኩ መለስተኛ ፕሮግራም ላይ «ከአማርኛ በተጨማሪ በበርካታ የአገሪቱ ሕዝብ የሚነገር ሌላ ቋንቋ የፌዴራሉ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ይደረጋል» በሚለው መካከል የጽንሰ ሃሳብም፤ የእምነትም ሆነ የአፈፃፀም አካሄድ ልዩነት የላቸውም ሁለቱም አገላለፆች በመሠረተ ሀሳብ አንድ ናቸው፡፡ የመድረኩ መለስተኛ ፕሮግራም ለየት የሚያደርገው የበርካታ የአገሪቱ ሕዝብ የሚነገር ቋንቋ ማለትና ይህም ኦሮምኛ ይሆናል የሚለውን ግምት ከመስጠቱ በስተቀር፡፡*

*የቋንቋ ፖሊሲ ሲወጣ ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች በርካታ ናቸው ከእነዚህም መካከል የቋንቋዎች ብዛት፤ የየአንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪዎች ብዛት፤ የየአንዳንዱ ቋንቋ የእድገት ደረጃ፤ አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ፤ የወላጆችና የተማሪዎች ፍላጎትና የግለሰብ መብትን ያካትታል፡፡ የተናጋሪዎች ብዛት ሲባል ደግሞ አንድን ቋንቋ በአፍ መፍቻ ቋንቋነትና በሁለተኛ ቋንቋነት*

የሚናገሩትን ደምሮ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ ሰዎች የሚኖሩበትን ክልል ቋንቋ መናገር የማይችሉ ከሆነ በሚችሉት ፌዴራል የሥራ ቋንቋ (ከሁለት በአንዱ) የሚማሩበት ወይም የሚሰሩበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል የሚል እምነት አለን፡፡

## 4. ምርጫ ዘጠና ሰባትን በሚመለት፡-

በመድረኩ መለስተኛ ፕሮግራም መግቢያ ላይ በገጽ 7 ላይ የተገለፀው ሃሳብ በአስተያየቱ እንደቀረበው ሁሉ በምርጫ 97 ዓም የተከፈለውን መስዋትነትና የተገኘውን ነገር ግን በጠመንጃ ኃይል የተቀለበሰውን የሕዝብና የቅንጅት ድል ተገቢ ቦታውን ያልሰጠ መሆኑን እውነት ነው፡፡ መግቢያው በተደጋጋሚ የተፃፈና በየጊዜው እየታረመ በመሄዱ አንዳንድ ነገሮችና አባባሎች ቀስ በቀስ እየተሸረሸሩ በመሄዳቸው የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ ብዙ ነገሮች ውስጥ ሲገባ አንዳንዱ ነገሮች ያመልጣሉ በመሆኑም ግድፈቱ ተፈጽሟል ወደፊት ግን በተገኘው አመቺ ሰዓትና ሁኔታ የሚስተካከልበትን መንገድ እናመቻቻለን፡፡ ይስተካከላልም፡፡

## 5. መሬትን በሚመለከት፤

በመድረክ መለስተኛ ፕሮግራም በገጽ 39 ተቁ 13.1 አርሶ አደሩ የሚጠቀምባቸው መሬቶች በራሱ በአርሶ አደሩ በግል ባቤትነት የሚያዝና አርሶ አደሩ ከመሬቱ የማይፈናቀልበት ሁኔታ የሚያረጋግጥ ይሆናል ይላል፡፡

13.3 ደግሞ ኢንቨስተሮች ከአርሶ አደሮች በግል ከተያዙት መሬት በመከራየት የሚያለሙት እንዲሆን ሊደረግ ይገባል ይልና

በ.ቁ 13.4 ከላይ በመድረኩ መለስተኛ ፕሮግራም የተጠቀሱትን ሃሳቦች ተቀብለን፡፡ በአንድነት እምነት ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ መሬት መሸጥ፤ መለወጥ፤ በውርስ ወይም በስጦታ ለሌሎች የማስተላለፍ መብት በሕግ የተጠበቀ ይሆናል፡፡ ይህም እምነት የከተማ መሬትም ላይም ተግባራዊ ይሆናል የሚለውን የፓርቲውን መርህ በልዩነት አስመዝግበናል፡፡